የመንፈቅ ዓመቱ እቅድ አፈጻጸማችን

ገጽ 3



ገጽ 6-7

መንግሥታችን ለዚህ ተቋም ትኩረት የመስጠት፣ ተገቢ የአመራር ድጋፍ የማድረግ፣ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ሥራዎችን አጠናክሮ ይቀጥላል።

አገራዊ ገቢው የተሰበሰበው እውቀት፣ ጉልበትና ጊዜ ወጥቶበት ብቻ ሳይሆን አካል ጎድሎበትና መተኪያ የሌለው ሕይወት ተከፍሎበት ጭምር ነው፡፡


# ገቢያችን ህልውናችን

አዳዲስ እና ትኩስ መረጃዎችን በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉ

ፌስቡክ:-
Ministry of revenues of Ethiopia
ዌብሳይት:-
www.mor.gov.et

12ኛ ዓመት | ቁጥር 147 | ጥር 2014 ዓ.ም | በነፃ የሚታደል







የ2013 በጀት ዓመት የላቀ የሥራ አፈጻጸም ተሸላሚዎች ሽልማታቸውን ሲቀበሉ፤

## ‹‹የጠንካራ ኢኮኖሚ ምንጩ ውጤታማ የግብር ሥርዓት ነው››

### - ምክትል ጠ/ሚ/ር ደመቀ መኮንን

የገቢዎች ሚኒስቴር በ2013 በጀት ዓመት የላቀ የሥራ አፈጻጸም ላሳዩ አመራሮችና ሠራተኞች እንዲሁም አካላት ጥር 21/2014 ዓ.ም. የኢፌዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በተገኙበት እውቅና እና ሽልማት ሰጥቷል። እውቅና እና ሽልማቱ የተሰጠው ለ216 ሠራተኞችና አመራሮች፣ ለ62 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሥራ ክፍሎች፣ ለሥራ ክፍሎች እና ለአንድ ተቋም እንዲሁም አገልግሎት አሰጣጡ በተሻለ የቴክኖሎጂ ደረጃ እንዲመራ ላስቻሉ ሦስት የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ነው።

አቶ ደመቀ፤ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ተጠሪ ለሆኑት ለጉምሩክ ኮሚሽን እና ለብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ሠራተኞች እና አመራሮች ሽልማትና እውቅናን ሲሰጡ እንዳሉት፤ ለጠንካራ ኢኮኖሚ ምንጩ ውጤታማ የሆነ የግብር ሥርዓት መገንባት በመሆኑ በተገኘው ውጤት መዘናጋት ሳይፈጠር መሥራትም እንደሚገባ አሳስበዋል።

ሃገራችን በጦርነትና ባለመረጋጋት ውስጥ ሆና የተመዘገበው ውጤት ተቋሙ ጠንካራ ሥራ እየሠራ መሆኑን የሚያሳይ ነው ያሉት ም/ጠ/ሚ/ሩ፤ ወደፊት ለሚጠብቀን የሃገር ግንባታ እና መልሶ ማቋቋሚያ ወጪ የሚሆን ከዚህም በተሻለ አፈጻጸም መሥራትን ይጠይቃል ብለው መንግሥትም ተቋሙን በተለየ ትኩረት እንደሚያግዘው አስታውቀዋል።

የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው በበኩላቸው፤ ምንም እንኳን ባለፈው ዓመት ሃገራችን አስቸጋሪ ፈተናዎች ያጋጠማት እና ችግሩ ወደዚህም ዓመት የዘለቀ ቢሆንም መላው የተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች ፈተናውን ተቋቁመው አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸው አስደናቂ ነው ብለዋል። በተያዘው በጀት ዓመትም ኮንትሮባንድን፣ ንግድ ማጭበርበርንና ግብር ስወራን በመከላከል ቀልጣፋና ዘመናዊ አሰራሮች በመዘርጋት ላይ በመሆናቸው እቅዳችንን በብቃት እናሳካለን ብለዋል።

የተቋማቱ ዋና መ/ቤቶች እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ባካተተው ሽልማት በላቀ የሥራ አፈጻጸም ለተመረጡት አመራሮችና ሠራተኞች ላፕቶፖችና ፍላት ስክሪን ቴሌቪዥኖች የተበረከቱ ሲሆን በተቋም ደረጃ ደግሞ የዋንጫ ሽልማት ተሰጥቷል።

**(በመርሐ-ግብሩ ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን እና የገቢዎች ሚኒስትር ላቀ አያሌው ያደረጓቸውን ንግግሮች በገጽ 6 እና 7 ላይ ይመልከቱ)**

## የዓለም የጉምሩክ ቀን ተከበረ

የዓለም የጉምሩክ ቀን በዓለም ለ39ኛ እና በሀገራችን ለሁለተኛ ጊዜ የ"በዳታ ባህል የታነፀ የዳታ ምህዳርን በመገንባት የጉምሩክ ዲጂታል ሽግግርን እናፋጥናለን!" በሚል መሪ ቃል ጥር 19/2014 ዓ.ም. በጉምሩክ ኮሚሽን ዋናው መ/ቤት ተከብሯል።

ኮሚሽኑ ከጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ዘመኑ የሚፈልጋቸውን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ለደንበኞች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ሰፋፊ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን የጉምሩክ ምክትል ኮሚሽነር አቶ አዘዘው ጫኔ ገልፀዋል። የዳታ ምህዳርን መገንባት፣ የዳታ ባህልን ማጎልበት፣ ደህንነትን

**የዓለም የጉምሩክ ቀን ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል**



በዓሉን ያከበሩት የጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮችና ሠራተኞች፤

## ሕይወታቸውን አሳልፈው ለሰጡ ሠራተኞች ቤተሰቦች የገንዘብ ድጋፍ ተደረገላቸው

በ2013 በጀት ዓመት ኮንትሮባንድና ህገ-ወጥ ንግድን በመከላከል ተግባር ላይ ተሰማርተው ሕይወታቸው ላለፈ ሠራተኞች ቤተሰቦች የገንዘብ ሽልማት ተሰጠ። ሽልማቱ የተሰጠው የገቢዎች ሚኒስቴር "አገልጋይነት መገለጫችን ነው" በሚል መሪ ቃል ለሠራተኞቹ እውቅና እና ሽልማት ባበረከተበት ወቅት ነው።

የሃገርና የህዝብን ሃብት አሳልፈን አንሰጥም በማለት ከህገ-ወጦች ጋር አንገት ለአንገት ተናንቀው ውድ ሕይወታቸውን መስዋዕት ላደረጉ ስድስት የተቋሙ

**ሕይወታቸውን ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

# ርዕሰ አንቀጽ

## በልጠው ስላገለገሏችሁ...

የሀገራችን ኢኮኖሚ እያመነጨ ያለውን ገቢ ያህል ከግብር የመሰብሰብ ብቃት ላይ ባንደርስም ወደዚያ እየወሰደን ያለውን መንገድ እያስመሩት ከሚገኙት ዋነኞቹ እናንተ መሆናችሁ ይታወቃል። ከናንተ መሀል ደግሞ በየዓመቱ በሕግ ተገዢነታቸው እና በገቢ አፈጻጸማቸው ለተሻሉት ሽልማት እየሰጠን እነብደሆነ እና ዘንድሮም ለ2013 በጀት ዓመት ተሸላሚዎች በየደረጃቸው ጥቅምት 24/2014 ዓ.ም. እውቅና እንደሰጠን ይታወቃል።

ለናንተ ስኬት እና ሀገር ከታክስ ለምትፈልገው ተገቢ ገቢ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ከሚገኙት መካከል ደግሞ የገቢው ዘርፍ ሠራተኞች እና አመራሮች ናቸው። ከነዚህ ሠራተኞች እና አመራሮች መካከል ደግሞ ለ216 ሠራተኞችና አመራሮች፣ ለ62 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ የሥራ ክፍሎች እና ተቋም እንዲሁም አገልግሎት አሰጣጡ በተሻለ የቴክኖሎጂ ደረጃ እንዲመራ ላስቻሉ ሦስት የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ልክ ለናንተ እንደተደረገው ጥር 21/2014 ዓ.ም. ሽልማት እና እውቅና ተሰጥቷል።

መ/ቤታችን ሠራተኞቹን እና አመራሮቹን በዚህ መልኩ ያበረታታ እንጂ ጥፋተኞች ሲያጋጥሙት ደግሞ የማያዳግም እርምጃ እንደሚወስድ ይታወቃል። ለአገልጋዮቻችሁ ክብር የምንሰጠው የናንተንም የአገልግሎት እርካታ መረጃ በመመርኮዝ ነውና በዚህም ልትመሰገኑ ይገባል።

ከዚህ ባሻገር ግን እንደተለመደው ብቻ ሳይሆን ከተለመደውም በላይ የሚጠበቅባችሁ ግብርን በወቅቱ እና በፈቃደኝነት ከመክፈል እንዲሁም በኮንትሮባንድና ሕገ-ወጥ ንግድ ላይ ካለመሳተፍ ግዴታ ባሻገር ለነዚህ ግዴታዎች ተገዢ የማይሆኑትን በመምከር፣ በማስተማር እና ባስ ካለ ለሕግ አካላት በመጠቆም ሀገራዊ ግዴታን መወጣት ይጠበቅባችኋል።

ይህን ተግባር ደግሞ መብታችሁ በሆነው በአግባቡ መስተንግዶ የማግኘት መብትም ላይ መፈጸም አለባችሁ። ከአንድ የገቢው ዘርፍ ሠራተኛ ሕጉ በሚፈቅደው ልክ አገልግሎት ካላገኛችሁ «ለምን?» የሚለውን ጥያቄ ከራሱ ከአገልግሎት ሰጪው አንስቶ በየደረጃው ለሚገኙ የሥራ መሪዎች በመጠየቅ መብታችሁን ማስከበር ይገባችኋል። ነገር ግን ነገሮችን በመሸፋፈንም ሆነ በቸልተኝነት ወይም በፍራቻ እና በ«ምን ቸገረኝ?»ነት ካለፋችሁ ዝምታው እንደበጎ ተግባር ተወስዶ ልምድ ይሆንና እናንተም ስትቸገሩበት ትኖራላችሁ፤ ሀገርም የምታተርፈው ነገር አይኖርም።

ስለዚህ፤ በልጠው ስላገለገሏችሁ የሸለምናቸው ሠራተኞች እና አመራሮች ከአሁን በብዙ እጥፍ እንዲበዙ የጠቆምናችሁን አካሄዶች እንድትከተሉ እናሳስባለን፤ ጥቅሙ፤ አንድም ለተሰማራችሁበት መስክ ማደግ፤ በሌላ መስኩ ደግሞ ከሀገር እድገት በሚገኘው ትርፍ የጋራችን ነውና!


ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- ወ/ሮ ኡሚ አባጀማል ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል
አቶ ዮሐንስ አዳሙ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጆች፡- ፀጥአርጋቸው ንጋቱ, ሕይወት ገ/መድህን, ራሔል ወልዴ, ሰዒድ ገልገሉ, በኃይሉ ሽመልስ, ሰለሞን ዘሪሁን

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 011-6-62-98-17 ፋክስ 011-6-67-39-14
ፖ.ሣ.ቁ 2559 ዌብሳይት www.mor.gov.et
ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia


## በመቶ ቀናት ውስጥ 81.7 ቢሊዮን ብር ይሰበስባል

ከጥር እስከ መጋቢት 30/2014 ዓ.ም. 81 ቢሊየን 775 ሚሊየን 217ሺ 581.18 ብር ገቢ ለመሰብሰብ በዕቅድ መያዙን የገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቁ። ሚኒስትሩ አቶ ላቀ አያሌው በማኅበራዊ ገጻቸው እንደገለጹት፤ ይህን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የገቢዎች ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮችና ሠራተኞች በተለመደው ቁርጠኝነትና ትጋት ይሠራሉ።

የተቋሙ ሠራተኞችና አመራሮች ቀልጣፋ አገልግሎትን ለደንበኞች በታማኝነት በመስጠት የአገርና የሕዝብ አደራን እንደሚወጡ እምነታቸውን ገልጸው «የሥራችን መነሻም ሆነ መድረሻ መለኪያ መስፈርቱ የአደባባይ ዲስኩር ሳይሆን የሕዝባችን የምስክርነት ቃል ነው» ብለዋል።

በመሆኑም፤ ሠራተኞቻችን የሕዝብ አገልጋይነትን ባለመዘንጋት፣ በሕዝብ ገንዘብና ጊዜ የራስን ከርስና ኪስ ባለመሙላት፣ ደምበኞችን በትህትና በማገልገል፣ የደንበኛን ንጉሥነትን በቃላት ሳይሆን በተግባር በማሳየት እና ሥራን ለነገ ባለማሳደር ለመሥራት የተለመደ ሥራቸውን ለመሥራት እየተጉ መሆናቸውን አመልክተዋል። በተጨማሪም፤ ጉዳዮችን ባለማንዛዛት፣ ባለጉዳዮችን ባለማጉላላት፣ ስንፍናንና ልግመኝነትን በማስወገድ እና በጉቦ፣ በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በጥቅም ትስስርና አካባቢን መሠረት ባደረገ አድልዎ ባለመሥራት ተግባራዊ ለማድረግ ቃላቸውን በየጊዜው እያደሱ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

እነዚህ ተግባራዊ ሲሆኑ ዕቅዳችንም ከመሳካትም በላይ ገቢ መሰብሰብ ስለሚቻል ግብር ከፋዮችም ሆኑ የተቋሙ ሠራተኞችና አመራሮች ከአሁን በፊት ያሳዩትን ትጋት የበለጠ እንዲደግሙት አሳስበዋል።

## ዲያስፖራዎች የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እየወሰዱ ነው

በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ሀገራዊ ጥሪ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ ለመጡ የዲያስፖራ አባላት የገቢዎች ሚኒስቴር ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በስካይ ላይት ሆቴል ባቋቋመው ጊዚያዊ አንድ አለቅ አገልግሎት መስጫ ማዕከል የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ሰጥቷል።

የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ በመስጠት ላይ ያለው ዲያስፖራዎቹ በአስመጭነት እና ላኪነት እንዲሁም በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ ለመሰማራት ያሳዩትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ እንደሆነ በገቢዎች ሚኒስቴር የደንበኞች ምዝገባና አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ዮሴፍ ሽፈራው ገልጸዋል።

አንድ ግብር ከፋይ በንግድ ሥራ ለመተዳደር እና ለመሰማራት ፈልጎ ሥራውን ሲጀምር ሕጋዊ ለመሆን የሚያስችለውን በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መያዝ ስለሚገባው የታክስ አስተዳደር አዋጁን በመመስረት አገልግሎቱ በሚኒስቴሩ ዋና መሥሪያ ቤት እየተሰጣቸው እንደሚገኝም ተናግረዋል።

በዚህም መሰረት ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የመጡም ዲያስፖራዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ እየተሰጠ ባለው አገልግሎት እንዲጠቀሙ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።



አመራሮች የ2014 ግማሽ በጀት አፈጻጸም ሪፖርት ሲከታተሉ፤

## የዓለም የጉምሩክ ቀን...

ከገጽ 1 የዞረ

ማስጠበቅ፣ ትብብር እና አጋርነትን ማጠናከር የጉምሩክ የመረጃ ስርዓት ግንባታን ለማጠናከር የሚያስችሉ የትኩረት ነጥቦች መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

ይህንንም እውን ለማድረግ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የትብብር ስምምነት ተደርጎ ወደ ሥራ መገባቱን አስታውቀው የዓለም አቀፉ የጉምሩክ ድርጅት ካስቀመጠው የአሠራር ሂደት ጋር የሚጣጣም የጉምሩክ ሥርዓት እየተፈጠረ መሆኑን አመልክተዋል።

በዕለቱ የዓለም ጉምሩክ ድርጅት አሠራር፣ አደረጃጀት እና ሕጋዊ ማእቀፎችን አስመልክቶ የውጭ ሀገር አጋርነት የሥራ ሒደት አስተባባሪ በሆኑት በአቶ አብርሀም ጉደታ ማብራሪያ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

በሥነ-ሥርዓቱ ላይ ከኮሚሽኑ ጋር ሲሠሩ ለነበሩና አመርቂ ውጤት ላሳዩ ባለድርሻ ተቋማት እና የኮሚሽኑ ሠራተኞች የእውቅና ሽልማት ተሰጥቷል።

ጽ/ቤቱን ቤልጂየም ብራሰልስ ያደረገውና 183 ሀገራትን በአባልነት የያዘው የዓለም አቀፉ የጉምሩክ ድርጅት የተቋቋመው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1973 ነው።

## አገልግሎቱን ዘመናዊ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ትኩረት ይደረጋል

ገቢዎች ሚኒስቴር በ2014 በጀት ዓመት የስድስት ወራት እቅድ አፈፃፀሙን የተቋሙ ኃላፊዎችና የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጆች በተገኙበት የገመገመ ሲሆን በቀጣይ በሚተኮርባቸው ጉዳዮች ላይ ተወያይቷል።

የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው፤ የግብር ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥና መረጃ አያያዝ ላይ የተሻለ ሥራ መሥራት የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራርን መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል። የግብር ከፋዮች የህግ ተገዥነት ደረጃና ታክስ ከፋዩ ሠርቶ ካተረፈው ገቢ በፈቃደኝነት አሳውቆ የመክፈል ዝንባሌ ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ ቢሆንም በየጊዜው አሳውቆ መክፈል ላይ የሚቀር ሥራ እንዳለ አስታውቀዋል።

ከሚከፈለውና በታክስ ኦዲት ሂደት ከሚገኘው ልዩነት አንጻር ገና ትልቅ ተግባር እንደሚጠበቅ የሚያመለክቱ ነገሮች ስላሉ የሕግ ተገዢነትን ማሳደግ ይገባል ብለዋል። በዚህም፤ የኦዲት ተደራሽነት፣ ጥራት እና ሙያዊ ብቃትን በማሳደግ የተጠናከረ የታክስ ኦዲት ሥራን መሥራት የግድ መሆኑን አመልክተዋል። እንዲሁም የግብር ከፋዩን የሰርቪስ ኦዲት ጥያቄ ሠራተኞችን በሟሟላት ተገቢውን ምላሽ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በተጨማሪም በሠራተኛው የሥራ ሥነ-ምግባር ላይ ሥራዎችን መሥራት፣ ለሠራተኛው እና ለግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ምቹ የሥራ አካባቢን በመፍጠር ሠራተኛው በሥራው ደስተኛ ሆኖ ግብር ከፋዩን እንዲያገለግል ማድረግ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰዋል። ግብር ከፋዩም በምቹ ቦታ ምቹ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል ከባቢን ማረጋገጥ እንዲሁም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ቁጥጥርና ክትትልን በተቀናጀ እና በተደራጀ መልኩ አትኩሮ በሚሠራበት ላይ አቅጣጫ ተቀምጧል።

## ሕይወታቸውን አሳልፈው ለሰጡ...

ከገጽ 1 የዞረ

ሠራተኞች ቤተሰቦች ለእያንዳንዳቸው የ75ሺ ብር የገንዘብ ድጋፍ ተበርክቶላቸዋል።

ድጋፉን ያበረከቱላቸው የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው ሕይወታቸውን መስዋእት ያደረጉት ሠራተኞች ጀግኖቻችን በመሆናቸው ለቤተሰቦቻቸው ከተደረገው የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘላቂነት ለማገዝ በዝግጅት ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

**(የተሸላሚዎቹን ዝርዝር እና ቤተሰቦቻቸው ሽልማታቸውን ሲረከቡ የሚያሳዩትን ፎቶዎች በገጽ 8 ይመልከቱ)**

# እንግዶችን

አዘጋጅ፡- ሕይወት ገ/መድህን

# የመንፈቅ ዓመቱ እቅድ አፈጻጸማችን

**ግብር በረጅሙ የአገራችን ታሪክ ውስጥ የነበረ፣ ዛሬም የአሠራር ሥርዓቱ ተሻሽሎና ተጠናክሮ የሚገኝ፣ ወደፊትም የሚቀጥል የአገሪት ሁሉ የጀርባ አጥንት ነው። በኛ ሀገር ደግሞ ይህንን ትልቅ አገራዊ አደራ ማለትም ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጠው ለገቢዎች ሚኒስቴርና ለተጠሪ ተቋማቱ ነው።**

**ሚኒስቴሩ ገቢ የመሰብሰብ አቅሙን በአሠራርና በቴክኖሎጂ እያዳበረ መጥቶ በ2013 በጀት ዓመት ለመሰብሰብ ካቀደው 290 ቢሊየን ብር 279.4 ቢሊየን ብር ገቢ ሰብስቧል። ይህም የእቅዱን 96.4 በመቶ ይሸፍናል። ገቢ የመሰብሰብ አቅሙን የማሳደጉ ማሳያ የሚሆነው በ2013 በጀት ዓመት የሰበሰበው ገቢ ከ2012 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ45.7 ቢሊየን ብር ብልጫ ማሳየቱ ነው።**

**ሚኒስቴሩ ገቢ የመሰብሰብ አቅሙን ካለፈው አመት የበለጠ በማሳደግ በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት የእቅድ አፈጻጸሙን ሀገር በብዙ ችግሮችም ውስጥ ሆና እያሳካ ይገኛል። ይህን አስመልክቶ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው የሰጡንን ማብራሪያ ቀጥሎ እናቀርባለን።**



**የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው፤**

**ያለፉት ስድስት ወራት የገቢ አፈጻጸም እንዴት ነበር?**

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የታክስ አሰባሰብ ሥርዓቱን በቴክኖሎጂና በአሠራር እያዘመነ በመምጣቱ በዚያው ልክ ገቢውም ከዓመት ዓመት እያደገ መጥቷል። በ2013 በጀት ዓመት 290 ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 279.4 ቢሊየን ብር፤ ማለትም የእቅዳችን 96.4 በመቶ መሳካቱ ሀገራችን ካሳለፈቻቸው የኮቪድ 19 ወረርሺኝ እና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከተካሄደው ጦርነት አኳያ አበረታች ነበር።

የኮሮና ወረርሽኝ ያደረሰውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ከባድ ነበር። አጠቃላይ የሀገራችን የንግድ እና የአገልግሎት ተግባሮች በተቀዛቀዙበት እና የሚኒስቴር መ/ቤቱም ተግባር የዚያኑ ያህል ተቀዛቅዞ በነበረበት ያንን ተቋቁመን ያስመዘገብነው ውጤት በፈተና ውስጥ ተሁኖ እንዴት ማለፍ እንደሚቻል ያስተምራል።

በአሸባሪው ሕወሓት የተከፈተው አገር የማፍረስ ጦርነት ደግሞ ብዙ አካባቢዎች ከሥራ ውጭ ሆነውና በሰሜኑ የአገራችን አካባቢ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶችንም ሥራ አቁመው እንደነበር ይታወቃል። ይህን አደጋ ለመከላከል የፀጥታ ኃይሎች የከፈሉት መስዋዕትነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች እና አመራሮች በትጋት በመንቀሳቀስ በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች ላይ በታክስ አሰባሰቡ እና በኮንትሮባንድ ቁጥጥሩ በትጋት በመሥራት አመርቂ ውጤት አስመዝግበናል።

እነዚህ ችግሮች በ2014 በጀት ዓመትም ቀጥለው በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠሩ ግጭቶች የንግዱ ማኅበረሰብ በሙሉ አቅሙ እንዳይሠራ በተደረገበት ብሎም በውጭ ምንዛሬ እና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት የገቢ ዕቃዎች ቢቀንሱም ባለፉት ስድስት ወራት የተሰበሰበው ገቢ በጣም ጥሩ ነው ብለን ለመናገር እንደፍራለን።

በመሆኑም በስድስት ወራቱ ውስጥ 185.7 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅደን 171.3 ቢሊዮን ብር ወይም የእቅዳችንን 92.21% መፈፀም ችለናል። ይህ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ስድስት ወራት አንጻር ሲታይ በብር 22.2 ቢሊዮን ወይም 14.9% እድገት ያሳያል።

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት አሰጣጥ እንዴት እየተከናወነ ነው?**

የገቢዎች ሚኒስቴርና የጉምሩክ ኮሚሽን ሠራተኞችና አመራሮች ሁሉንም ፈተናዎች ተቋቁመው የተሻለ ገቢ እንዲሰበሰብ አድርገዋል። ይህንን ያደረጉት ከልብ የመነጨ አገራዊ ስሜት ስላላቸው ነው እንጂ ሰበቦችን ለማብዛትና ምክንያቶችን ለመደርደር ወቅቱ የተመቸ ነበር። ነገር ግን ይህን ሰበብ ሳያደርጉ ብዙዎቹ በእረፍት ቀናቸው፣ (ጠዋትና ማታ፣ ቅዳሜና እሁድ ጭምር እንዲሁም በዓላትንም) ያለእረፍት ሠርተዋል።

በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮችና ሠራተኞች በየመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ሳምንቱን ሙሉ ለ24 ሰዓት መሥራት ብቻ ሳይሆን ሕይወትና አካላቸውን ገብረዋል። በታክስ አሰባሰብ ላይ ደግሞ በተለይ በየወሩ መጨረሻ እና በወቅታዊዎቹ ግብርን አሳውቆ የመክፈያ ጊዜያት (ከሐምሌ 1 እስከ ታኅሣሥ 30 ዓመታዊ የግብር መክፈያ ግዴታ መወጫ መጨረሻ ቀናት ላይ) ያለእረፍት የሰቷቸው አገልግሎቶች ቀላል አልነበሩም። እነዚህ የሁለቱ ተቋማት ተግባራት በቀጣይም ተጠናክረው የሚቀጥሉ ናቸው።

እነዚህ ውጣውረዶች ወይም ድካሞች የሚያሳዩት የተሰበሰበው ገቢ የእውቀት፣ የጉልበት፣ የጊዜ የአካል መጉደል እና መተኪያ የሌለው ሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ውጤቶች መሆናቸውን ነው።

በአገልግሎት አሰጣጣችን በተቻለ መጠን ደንበኞች እንዳይረሩ ነው እየሠራን ያለነው። ከደንበኞቻችን ጋር ስንገናኝ ከ‹‹መጣብኝ›› ወይም ‹‹መጣችብኝ›› ይልቅ ‹‹መጣልኝ›› ወይም ‹‹መጣችልኝ›› እንድንባል ነው እየሠራን ያለነው። በዚህ መንፈስ አገልግሎት የማይሰጡ እንዳይኖሩ ደግሞ ከሚሠሩባቸው የሥራ ክፍሎች በተጨማሪ በየደረጃው በሚገኙ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች በኩል ቁጥጥር፣ ክትትል እና ችግር ያለባቸው ሲያጋጥሙ እርምጃ ይወሰዳል።

በአጠቃላይ፤ ባለጉዳዮች ተቸግረውና ከእኛ መፍትሔ ፈልገው ሲመጡ መርዳትና ማገዝ፣ በቅን ልቦና እና በንጹህ እጅ መሥራትም ግዴታችን ነው። ይህ ከሆነ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ስለተቋሞቻችን በአደባባይ ይመሰክራሉ። የመጨረሻው የስኬታችን መለኪያና መስፈርትም የእኛ የአደባባይ ድስኩር ሳይሆን የሕዝባችን የምስክርነት ቃል ነው።

**ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት በኩል ስለተሠሩ ተግባራት ቢገልጹልን?**

የተቋማችን አመራሮችና ሠራተኞች መደበኛ ሥራቸውን በአግባቡ ከመሥራት ጎን ለጎን ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ። በዚህም መሠረት ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ከ1.126 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደርጓል።

የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፤ በየወሩ ከወር ደመወዝ በሚቆረጥ ገንዘብ ከ200 በላይ ወገኞችን በቋሚነት እየረዳን እንገኛለን። ከ112 በላይ ቤቶችን በማደስ ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወገኖች አስረክበናል፤ ለሀገር መከላከያ ሠራዊት ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት ደም እየለገስን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ አመራሮችና ሠራተኞች የወር ደምወዛችንን ገበታ ለአገርና ለመከላከያ ሠራዊት አዋጥተናል። እንዲሁም ጉምሩክ ኮሚሽን በየጊዜው ከሚይዛቸው የኮንትሮባንድ ቁሳቁሶች መካከል ለሰው ሠራሽና ለተፈጥሮ አደጋ የተጋለጡ ወገኞችን እርዳታ ሰጥተናል።

በ2013 በጀት ዓመት የተሻለ የሥራ አፈፃፀም ላሳዩ ሠራተኞችና አመራሮች ሽልማት ስንሰጥ የሃገርና የህዝብን ሃብትና ንብረትን ለኮንትሮባንዲስቶች አሳልፎ ላለመስጠት ሲታገሉ ሕይወታቸውን ላጡ ሠራተኞች ቤተሰቦች የገንዘብ ድጋፍ አድርገናል። እነዚህን ቤተሰቦች ገንዘብ ሰጥቶ መሸኘት ብቻ ሳይሆን በዘላቂነት ለማገዝ በዝግጅት ላይ ነን።

**የቀጣይ ስድስት ወራት ትኩረት ምን ይመስላል?**

በቀሪዎቹ ስድስት ወራት በመጀመሪያው ስድስት ወራት ካስመዘገብነውን ውጤት የበለጠ ስኬታማ ለማድረግ የአሠራር ሥርዓታችንን ከማዘመን ባሻገር የአሠራር ልህቀታችን ላይ ልዩ ትኩረት እንሰጣለን። ለዚህም የአገልጋይነት ሰብዕናን በመላበስ አገልግሎታችንን ተገልጋይ ተኮር፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ቀላል፣ ለደንበኞቻችንም መንገድ ቀያሽና ፍሰቱ የተቀላጠፈ እንዲሆን በቁርጠኝነት እንሠራለን።

በሌላም በኩል የአሠራር ግድፈቶችንና ችግሮችን ለይቶ በማረምና ዘላቂ መፍትሄ በመስጠት የማስተማርና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ እንሠራለን።

**በቀጣይ ከግብር ከፋዮች ምን ይጠበቃል?**

ግብር ከፋዮች ኮንትሮባንድን፣ የንግድ ማጭበርበርን፣ ግብር ስወራንና ማሸሸን፣ ደረሰኝ አለመቁረጥን፣ ከሐሰተኛ ደረሰኝና ከሐሰተኛ ማንነት ጋር ተያይዞ የሚሠሩ ወንጀሎችን መጸየፍ አለባቸው። በዚህ ደግሞ ራሳቸውን አርዓያ ማድረግ የመጀመሪያ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል። ሌላው ደግሞ፤ በነዚህ ሕገ-ወጥ ተግባራት ላይ የተሰማሩት ሲያጋጥሟቸው መከላከል እና ለሚመለከታቸው አካላት በመጠቆም ሀገራዊም ሆነ የዜግነት ሚናቸውን መጫወት አለባቸው። እነዚህን ሚናዎች ገቢን ለመሰብሰብ ሙሉ ጊዜያቸውን ሰውተው እየተጉ ከሚገኙት የገቢው ዘርፍ ሠራተኞች ጋር በመሆን ሊፈጽሙ ይገባል።

ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ- ሰለሞን ዘሪሁን

# ስለማንዋል ደረሰኝ

የማንዋል ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፣ ደረሰኙ ሊይዝ የሚገባቸው ዝርዝር መረጃዎች፣ ደረሰኙን የሚጠቀም ታክስ ከፋይ ኃላፊነት፣ ደረሰኙን የሚያትመው ማተሚያ ቤት ኃላፊነት፣ "ደረሰኙ ጠፋብኝ" ለሚለው ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ እና ከደረሰኝ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ ወንጀሎች ምንድን ናቸው? የሚሉ ዝርዝር መረጃዎችን "የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011"ን በማጣቀስ እናቀርባለን።

የማንዋል ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

ሀ. በኢንቨስትመንት ሂደት ላይ ያለና የንግድ ሥራ ያልጀመረ ከሆነ ከተከፋይ ሂሳብ

ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ ለማሳተም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና የኢንቨስትመንት ሰርተፊኬት፤

ለ. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ውክልና የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ መሥሪያ ቤቶች ወይም ግለሰብ ነጋዴዎች ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ ለማሳተም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤

ሐ. የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላወጣና የመደበኛ ሽያጭ ያልጀመረ ሰው የሙከራ ምርት ለመሸጥ ወይም ከግንባታ ሥራ የተረፈ ዕቃ ለመሸጥ የሚያገለግል ደረሰኝ ለማሳተም ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) ከተገለጸው በተጨማሪ ምክንያቱን የሚገልፅ ደብዳቤ፤

መ. በንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ታክስ ከፋይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ሕጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና ምዝገባ ምስክር ወረቀት (ሰርተፊኬት)፤

ሠ. የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ወኪል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ አለበት።

I. በንግድ ሥራ ላይ የተሠማራም ሆነ ያልተሠማራ ሰው በሚታተመው ደረሰኝ ላይ የድርጅቱ የንግድ ምልክት (logo) እንዲካተት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክቱ የተመዘገበበትን ማስረጃ፤

II. በተራ ቁጥር (I) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ደረሰኝ ለማሳተም ጥያቄ የሚያቀርበው ሰው በሚታተመው ደረሰኝ ላይ የንግድ ስም እንዲጠቀስ በሚፈለግበት ጊዜ የንግድ ስም ምዝገባ ምስክር ወረቀት፤

III. ከላይ በተራ ቁጥር (I) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የደረሰኝ ህትመት ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው የማንዋል ደረሰኝ ሊይዝ የሚገባውን መረጃ ያካተተ እና ማሳተም የሚፈለገውን የደረሰኝ ብዛት፣ የዓይነት እና ናሙና፤

IV. ማንኛውም ደረሰኝ ለማሳተም ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ለማሳተም የሚፈልገውን የማንዋል ደረሰኝ ዓይነትና ብዛት ከደረሰኝ ናሙናው ጋር በደረሰኝ ህትመት መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ ላይ በመሙላት ታክስ ለሚከፈልበት ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል።

የማንዋል ደረሰኝ ሲታተም ቢያንስ የሚከተሉትን መሠረታዊ መረጃዎች ሊይዝ ይገባል:-

- የአቅራቢው ሙሉ ስም፣ አድራሻና የተመዘገበ የንግድ ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ተመዝጋቢ ከሆነ) ቁጥሩና ለታክሱ የተመዘገበበት ቀን እና የደረሰኙ ተከታታይ ቁጥር አስቀድሞ የታተመበት (Pre-Printed)፤
- የገዢው ሙሉ ስም፣ አድራሻና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መመዝገቢያ፣ የተሸጠው ዕቃ ወይም የተሰጠው አገልግሎት ዓይነትና የገንዘብ መጠን እንዲሁም በሽያጭ ፖሊሲ ወይም በውል ምክንያት የተደረገ የሽያጭ ቅናሽ ገንዘብ መጠን የሚገለፅበት ክፍት ቦታ ያለው፤
- ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ የሚፈለገውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የተርን ኦቨር ታክስ ገንዘብ መጠን፣ በፊደል እና በአሃዝ የተፃፈ ጠቅላላ የሽያጭ ወይም ግብይት ዋጋ የገንዘብ መጠን እንዲሁም ደረሰኙ የተሰጠበት ቀን የሚገለፅበት ክፍት ቦታ ያለው፤
- ደረሰኙን ያዘጋጀው ወይም ገንዘቡን የተቀበለው ሠራተኛ ስምና ፊርማ የሚሰፍርበት ክፍት ቦታ፤
- የደረሰኝ አታሚው ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ደረሰኙ የታተመበት ቀንና የአታሚው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቁጥር እና የአታሚው ስልክ ቁጥር እንዲሁም የሽያጭ ደረሰኙ እንዲታተም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደበትን ደብዳቤ ቁጥርና ቀን አስቀድሞ የታተመ (Pre-Printed)፤ የሚሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል።

**የማንዋል ደረሰኝ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ ኃላፊነት**

ማንኛውም የማንዋል ደረሰኝ እንዲጠቀም የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩበታል።

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ እና ዕውቅና ያልተሰጣቸውን ደረሰኞች አለመጠቀም፤
- ለአንድ ግብይት ጥቅም ላይ የዋለን ደረሰኝ ለሌላ ግብይት አለመጠቀም፤
- በበራሪና ቀሪ ቅጠሎች ላይ የተለያየ መረጃ አለመመዝገብ፤
- ግብይቱ ከተከናወነበት ሽያጭ ዋጋ የተለየ የገንዘብ መጠን በደረሰኙ ላይ አለማስፈር፤
- የደረሰኝ ህትመት ከተፈቀደለት ግብር ከፋይ ውጪ ለሌላ ታክስ ከፋይ ጥቅም ላይ እንዲውል አለማድረግ፤
- ያለደረሰኝ ሽያጭ አለማከናወን፤
- ደረሰኝ ለሚጠይቁ ግዥ ፈፃሚዎች ሽያጭ አለመከልከል፤
- ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ በማሳተም ጥቅም ላይ አለማዋል፤
- እንዲሰረዝ ውሳኔ በተሰጠበት ደረሰኝ አለመጠቀም፤
- ደረሰኝ ሲታተም ዝርዝር መረጃዎችን አሟልቶ የያዙ ደረሰኞችን አሳትሞ መጠቀም፤
- በራሪና ቀሪ ቅጠሎች ያለው ደረሰኝ ማሳተም፣ ደረሰኞችን በጥንቃቄ መያዝ እና ግብይት የተፈጸመባቸውን ደረሰኞች በታክስ አዋጁ እስከተገለፀ ጊዜ ድረስ ይዞ ማቆየት፣ ለሒሳብ ምርመራ ወይም ለግብር አወሳሰን እንዲቀርብ በሚጠየቅበት ጊዜ ማቅረብ፤
- የደረሰኝ አጠቃቀም መከታተያ ሌጀር ለሁሉም በግልጽ በሚታይበት ቦታ መስቀል እና ትክክለኛ መረጃ እንዲይዝ ማድረግ ይጠበቅበታል።

የማንዋል ደረሰኞችን የሚያትም ማተሚያ ቤት ኃላፊነቶች

i. ለታክስ ዓላማ የሚውል ደረሰኝ ለማተም የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመያዝ፤

ii. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ደረሰኝ ለማሳተም ወደ ማተሚያ ቤቱ ሲመጣ:-

- ታክስ ከፋዩ ደረሰኝ እንዲያሳትም ከታክስ መ/ቤቱ ደብዳቤ የተፃፈለት መሆኑን እና
- የህትመት ጥያቄውን ያቀረበው ሰው ታክስ ከፋዩ ራሱ ወይም ወኪሉ መሆኑን የማረጋገጥ እንዲሁም
- በቀረበለት ደረሰኝ ማንዋል ላይ ደረሰኝ እንዲታተም ፈቃድ የተሰጠው የታክስ መ/ቤት ማህተም መኖሩን የማረጋገጥ፤

iii. በቀረበለት ደረሰኝ ናሙና ላይ የተመለከቱ መረጃዎች በሚታተመው ደረሰኝ ላይ እንዲካተቱ የማድረግ፤

iv. የደረሰኞቹን ቁጥር ተከታታይነት የማረጋገጥና ምስጢራዊ መለያ ሰጥቶ የማተም እንዲሁም በማንኛውም ሁኔታ ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ በድጋሜ እንዳይታተም ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ፤

v. የደረሰኝ ህትመት ጥራትን የማሟላት፤

vi. የህትመት አገልግሎት የተሰጣቸውን ታክስ ከፋዮች ዝርዝር የያዘ ሪፖርት በየሩብ ዓመት (በየሦስት ወሩ) ታክስ ለሚከፍልበት ቅ/ጽ/ቤት የማቅረብ፤

vii. የህትመት አገልግሎት የሚሰጥበትን አድራሻ ሲቀይር ታክስ ለሚከፍሉበት ቅ/ጽ/ቤት የማሳወቅ፤

viii. በማተሚያ ቤቱ ክፍያ ሲፈፀምለት በሚሰጠው ደረሰኝ ላይ የታተመውን ደረሰኝ ዓይነትና ሴሪያል (ከ...እስከ) ቁጥር የመስጠት ግዴታ አለበት።

የማንዋል ደረሰኝ ጠፋብኝ ጥያቄ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቀባይነት የሚያገኝበት ሁኔታ

i. ታክስ ከፋዩ ያሳተመው ደረሰኝ የጠፋው ወይም ከጥቅም ውጪ የሆነው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

ii. ከላይ በተራ ቁጥር i የተመለከተውን ማስረጃ ማቅረብ ያለበት ከፖሊስ ጣቢያ፣ ከፍርድ ቤት ወይም ከእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ኤጀንሲ እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ይሆናል።

iii. ደረሰኙ ስለመጥፋቱ ወይም ከጥቅም ውጪ ስለመሆኑ ሦስተኛ ወገን እንዲያውቀው መጥፋቱ ወይም ከጥቅም ውጪ መሆኑ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና ቴሌቪዥን ወይም ሬዲዮ ማስታወቂያ ማስነገር ይኖርበታል።

iv. ከላይ በተራ ቁጥር iii ለተነገረው ማስታወቂያ ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ በአስር ቀን ውስጥ ለታክስ መ/ቤቱ መቅረብ አለበት።

v. ከላይ በተራ ቁጥር iv መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማስታወቂያ ማስረጃው ሲቀርብለት ደረሰኙ የጠፋው ወይም ከጥቅም ውጪ የሆነው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ ታክስ ከፋዩ ደረሰኙን ያልሠራበት ስለመሆኑ የሚገልፅ ማረጋገጫ ይሰጣል።

vi. ከላይ በተራ ቁጥር v የተመለከተው ማረጋገጫ ለታክስ ከፋዩ ቢሰጥም ማረጋገጫው ከተሰጠ በኋላ በማንኛውም ሁኔታ ታክስ ከፋዩ በደረሰኙ ተጠቅሞ ከተገኘ በሕግ እንዲጠየቅና ደረሰኙን በተጠቀመበት ገቢ ላይ የታክስ መ/ቤቱ ታክስ መወሰን አለበት።

vii. የታክስ መ/ቤቱ የጠፋውን ወይም ከጥቅም ውጪ የሆነውን ደረሰኝ የሚመለከቱ መረጃዎችን ታክስ ለሚከፍልበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመረጃ ሥርዓት በማስገባት እንዲያውቁት ያደርጋል።

viii. ታክስ ከፋዩ ያሳተመው ማንኛውም ደረሰኝ የጠፋ ወይም ከጥቅም ውጪ የሆነ መሆኑን ታክስ ከፋዩ ከማወቁ በፊት በማንኛውም ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረሰበት እንደሆነ ደረሰኙ በማንኛውም ሁኔታ ጥቅም ላይ አለመዋሉን ማረጋገጥ ካልቻለ ታክስ ከፋዩ በደረሰኙ እንደተጠቀመ ተቆጥሮ ታክስ ይወሰናል።

ix. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ እና የግዥ ማረጋገጫ ሰነድ (Purchase Voucher) በተለያየ ምክንያት ሲጠፋ ወይም ከጥቅም ውጭ ሲሆን ታክስ ከፋዩ ደረሰኙ ስለመጥፋቱ በብዙሃን መገናኛ ማስታወቂያ ማስነገር ሳያስፈልገው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

x. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ማለት ታክስ ከፋዩ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያት የተከሰተ ጦርነት፣ ዝርፊያ፣ ጎርፍ፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅና የመሳሰሉት ናቸው።

ከደረሰኝ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ ወንጀሎች

I. ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺ) እስከ ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ) የገንዘብ መቀጫ እና ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

II. በአንድ ግብይት በተሰጡ ተመሳሳይ የደረሰኝ ኮፒዎች ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሽያጭ ዋጋን ያሳነሰ ማንኛውም ሰው ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) እና ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

III. የሽያጩ ትክክለኛ ዋጋ ከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) የሚበልጥ ከሆነ በዚህ ተራ ቁጥር ‖ መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኞቹ ላይ ከተመለከቱት ከፍተኛው የገንዘብ መጠን እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

IV. ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሰጠ ወይም የተቀበለ ሰው ከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) እስከ ብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

V. በዚህ ተራ ቁጥር IV የተመለከተው ደረሰኝ ከብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) የሚበልጥ የገንዘብ መጠን የያዘ እንደሆነ በዚህ ተራ ቁጥር | መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኙ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደረስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

VI. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳይፈቅድለት የታክስ ደረሰኝ ያተመ ሰው ከብር 300,000.00 (ሦስት መቶ ሺ) እስከ 500,000.00 (አምስት መቶ ሺ) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሁለት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

VII. ከላይ በተራ ቁጥር (VI) መሠረት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ወንጀሉን ለሁለተኛ ጊዜ ፈፅሞ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ የህትመት መሣሪያው እና የማተሚያ ድርጅቱ ይወረሳል፣ የንግድ ፈቃዱም ይሰረዛል። ስለሆነም ህጋዊነትን ተከትለን የንግድ ሥራችንን እናከናውን።



# በየዓይነቱ

አዘጋጅ፡- በኃይሉ ሺመልስ

## ፎቢያዎች (Phobias)

ፎቢያ ለአንድ ነገር ወይም ሁኔታ ምክንያታዊ ያልሆነ ከፍተኛ ፍርሀት ማለት ሲሆን የአንዳንድ ሰዎችን ህይወት ከባድ ሊያደርገው ይችላል።

ፎቢያዎች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና ሊያሳድሩ ይችላሉ። ነገር ግን ብቻዎን እንዳልሆኑ ያስታውሱ። ከመቶ ሰዎች አስሩ የሆነ ዓይነት ፎቢያ እንደሚኖራቸው ጥናቶች ያሳያሉ። ያለመድሐኒት በንግግር ህክምና (Psychotherapy, specifically behavioral therapy) ሊታከሙ ይችላሉ፤ ያለአእምሮ ጤና የለምና!

- አኩሎፎቢያ (Achulophobia)፡- የጨለማ ፍርሀት
- አክሮፎቢያ (Acrophobia)፡- የከፍታ ፍርሀት
- አውቶፎቢያ (Autophobia)፡- የብቸኝነት ፍርሀት
- ክላስትሮፎቢያ (Claustrophobia)፡- ትፍግፍግ ያለ ቦታ ፍርሀት
- ሳይኖፎቢያ (Cynophonia)፡- የውሻ ፍርሀት
- ኢሉሮፎቢያ (Elurophobia)፡- የድመት ፍርሀት
- ጋሞፎቢያ (Gamophobia)፡- የትዳር ፍርሀት
- ሄሞፎቢያ (Hemophobia)፡- የደም ፍርሀት
- አያትሮፎቢያ (Iatrophobia)፡- የዶክተር ፍርሀት
- ሎኪኦፎቢያ (Lockiophobia)፡- የምጥና የመውለድ ፍርሀት
- ሙሶፎቢያ (Musophobia)፡- የአይጥ ፍርሀት
- ኔክሮፎቢያ (Necrophobia)፡- የሞተ ነገር ፍርሀት
- ኦፊዲኦፎቢያ (Ophidiophobia)፡- የእባብ ፍርሀት
- ፓቶፎቢያ (Pathophobia)፡- መታመምን መፍራት
- ፊሎፎቢያ (Philophobia)፡- የፍቅር ፍርሀት
- ፎቦፎቢያ (Phobophobia)፡- የፍርሀት ፍርሀት
- ፖለቲኮፎቢያ (Politicophobia)፡- የፖለቲከኞች ወይም የፖለቲካ ሂደት ፍርሀት
- ስኮሊኦኖፎቢያ (Scolionophobia)፡- የትምህርት ቤት ፍርሀት
- ትሪፓኖፎቢያ (Trypanophobia)፡- መርፌ የመወጋት ፍርሀት
- ታናቶፎቢያ (Thanatophobia)፡- የሞት ፍርሀት
- ዜኖፎቢያ (Xenophobia)፡- መጤ የሆነ ሰው ፍርሀት

Source:- ድሬ ትዩብ ዶ/ር ዮናስ ላቀውን ጠቅሶ እንደጻፈው




## «አባት ሳለ አጊጥ፤ ጀንበር ሳለች ሩጥ!»

ይህ ወጣት አብሮት ስለቆመው አባቱ የጻፈው ልብ የሚነካ መልዕክት ነው።

"የኔ ጣፋጭ አባት ሁሴን፤ እናቴ ሴምፒጃ ከተገደለች ጀምሮ የአዕምሮ መታወክ ህመም አለበት። በጓደኞቼ እየተሰደብኩ ነው ያደግሁት። ‹አባትህ አብዱል› ይሉኛል። ግን አላፍርበትም ነበር። ምክንያቱም፤ እማዬ ከሞተች ጀምሮ ያሳደገኝ እነርሱ ‹‹አብዱል›› ብለው የሚሰድቡት ድሃው አባቴ ነው። ሁሌም ትቶኝ አያውቅም። ለዛም ነው፣ ‹‹አባቴ ደፋርና ጀግና ሰው ነው›› የምለው። አባዬ፤ እወድሃለሁ፤ አንተም አባቴ ስለሆንክ መቼም አላፍርብህም፤ እግዚአብሔር ትልቅ ምክንያት አለውና!" ይላል።

## እውነተኛ ባለጠግነት እና እውነተኛ ሥልጣን ራስን መሆን ነው



አባቱ ጫማ ሰፊ የሆነው አብርሐም ሊንከን የአሜሪካን ፕሬዚደንት በሆነ ጊዜ ሀብታም ከሆኑት ሰዎች፣ የላቀ ደረጃ ካላቸው ሰዎች፣ ከተከበረና ዝነኛ ሆኖ ከኖረ ቤተሰብ በመምጣታቸው የበላይነት ስሜት ያላቸውን ሰዎች በሙሉ የጫማ ሰሪ ልጅ ከአናት ሆኖ ሲያዛቸው የሀፍረት ስሜት ተሰምቷቸው ነበር። ሊንከን ፕሬዚደንት በመሆኑ በሙሉ መሸማቀቅ፣ ቁጣ እና ብስጭት አጠላባቸው እንጂ ደስተኛ የነበረ ሰውም የለም።

ሊንከን የመጀመሪያ ንግግሩን ለሕግ መወሰኛ ምክር ቤት በሚያቀርብበት ጊዜ አንዱ ዘላፊ የሆነ ሰው ተነስቶ፣ "ሚ/ር ሊንከን፣ ንግግርዎን ከመጀመርዎ በፊት የጫማ ሰሪ ልጅ መሆንዎን ላስታውሶት እወዳለው" አለው። ያን ጊዜ ሴኔቱ በሙሉ ሳቀ። ሊንከንን ሊያሸማቅቁት ፈልገው ነበረ። ሆኖም ሊያሸንፉት አይችሉም። ነገር ግን እንዲያፍር ሊያደርጉት ይችላሉ። ይሁን እንጂ እንደ ሊንከን ያለውን የሕይውት ስንክሳር አይቶ ወደ ስልጣን የመጣን ሰው እንዳያፍር ለማድረግም እጅግ አስቸጋሪ ነው። ሊንከን ሰውየውን፣ "አሁን በሕይወት የሌለውንና ጫማ ሰሪ የነበረውን አባቴን ስላስታወስከኝ እጅግ ከፍ ያለ ደስታ ይሰማኛል። የሰጠኸኝን ምክር ምንጊዜም አልረሳውም። ጫማ ሠሪው አባቴ ባይሆን ኖሮ እንደዚህ ታላቅ ፕረዚደንት መሆን እንደማልችል ጠንቅቄ አውቀዋለሁ" አለ። ፍጹም ፀጥ ረጭ ያለ ሁኔታ ተፈጠረ። ሊንከን ንግግሩን ቀጠለ...፤

"እስከማውቀው ድረስ ለአንተም ቤተሰቦች ቢሆን አባቴ ጫማቸውን ይሠራላቸው ነበር። ትልቅ ጫማ ሠሪ ባልሆንም ገና ከልጅነቴ ጀምሮ ከአባቴ ዘንድ ጥበብን ስለተማርኩ ጫማዎችህ ሲያልቁም ሆነ ችግር ሲያጋጥምህ ላስተካክልልህ እችላለሁ። እንዲሁም አባቴ ጫማ ይሠራ ስለነበረ የሚሰፋና የሚስተካከል ካላችሁም እዚህ ሴኔት ውስጥ ላላችሁት ለማንኛችሁም ለመሥራት ዝግጁ ነኝ። ሆኖም ግን አንድ ነገር እርግጠኛ ሁኑ፤ እንደ አባቴ ግን ፍጹም አይደለሁም። የእርሱ ሥራ ፍፁም ወርቅ ነው" ሲል ተናገረና አባቱን እያሰበ ዐይኖቹ በእንባ ታጠቡ።

አንተ ከተራ ቤተሰብ የወጣህ፣ ፕሬዝዳንትም ሁን አልያም አንደኛ የተባልክ ጫማ ሠሪ፤ ልዩነት አያመጣም። ቁም ነገር ያለው የምትሠራውን ሥራ በፍላጎት መሥራተህ እና ያለህን ጉልበት ሁሉ እዛ ላይ ማዋልህ ነው። ራስህን እንጂ ማንንም ሰው ለመሆን መፈለግ የለብህም። በዚህም ጊዜ ተፈጥሮ በድራማ ውስጥ የሰጠችህን ክፍል በደንብ ለመጫወት ከተፈጥሮ ጋር ትስማማለህ። ያን ጊዜ ንጉሥም ሆነ ፕሬዚዳንት ለመሆን ራስህን አትቀይረውም። በጥቅሉ፤ "እውነተኛ ባለጠግነት እና እውነተኛ ሥልጣን ራስን መሆን ነው"።

## ከሰው ምን...

በዝናብ ነው ማልቀስ
እየበሰበሱ፣
ጎርፍ እየጠረጉ
ቦይ እያፈሰሱ፡፡
በዝናብ ነው ማልቀስ
ከሰው ተከልሉ፣
ፈጣሪ እንዲሰማ
እንዲደርሰው ቶሉ፡፡
በዝናብ ነው ማልቀስ
ፊትን እያጠቡ ገላ እያጠመቁ፣
እያመነመኑ፣
ምቀኛ ካልበዛ
በዚህም ካልቀኑ፡፡

የሺወርቅ ተጫነ (በ2013 ዓ.ም.
«ክረምት እንታረቅ» በሚል
ካሳተመችው የግጥም መድብል መጽሐፍ)

**ጥር 21/2014 ዓ.ም. የገቢዎች ሚኒስቴር በ2013 በጀት ዓመት በአፈጻጸማቸው የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ሠራተኞቹ እና አመራሮቹ እንዲሁም አካላት እና በኮንትሮባንድ መከላከል ተግባር ላይ ላሉ ሕይወታቸው ላለፈ ሠራተኛ ቤተሰቦች ሽልማት እና እውቅና ሰጥቶ ነበር። ሽልማቱን እና እውቅናውን የሰጡት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የአስቱ የክብር እንግዳ አቶ ደመቀ መኮንን እንዲሁም የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው ሲሆኑ በእለቱ ያደረጓቸውን ንግግሮች ቀጥለን እናቀርባለን።**




**... ጠንካራ ኢኮኖሚ የገነቡ እና ዓለምን የሚዘውሩ ሀገሮች አንዱ የስኬታቸው ምንጭ በገቢ ላይ ያላቸው ውጤታማነት፣ የአስተሳሰብ አንድነት እና የትውልድ ቅብብሎሽ ነው...**

## የምክትል ጠ/መ/ር ደመቀ መኮንን ንግግር

ባሳለፍናቸው ጊዜያት ሀገራችን በርካታ ውጪያዊና ውስጣዊ ጫናዎችን በመቋቋም ሉዓላዊነቷን፣ ኅብረቷን እና የግዛት አንድነቷን አስጠብቃ በሒደት ዘላቂ ሰላምና ዕድገት ለማረጋገጥ በመረባረብ ላይ ትገኛለች። ታሪክ እንደሚያስረዳውና አሁንም በተግባር እንደምናየው ሀገራችን በሉዓላዊነታቸው ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችን እና በማንኛውም ጊዜ የሚቃጡ ጥፋቶችን አስመልክቶ መቼም ቢሆን የማትደራደርበት ጉዳይ ከመሆኑ ባሻገር ጠላቶቿን አሳፍራ በመሸኘቷ የመቆም ልምዷ ያለ ነው።

ዛሬም ቢሆን በዚህ ትውልድ እና ዘመን ሀገራችን በየአቅጣጫው ውስብስብ ጫናዎች እየደረሱባት በመሆኑ መንግሥታችን እና ሁሉም ዜጎች ይህንን ለመመከት ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ሆነው በጋራ የአሸናፊነት ማማ ላይ እየወጡ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ሀገራዊ አንድነት ለመገንባት፣ ሉዓላዊነቷን በማስቀጠል እና የግዛት አንድነቷን በማስጠበቅ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችን በዘላቂነት የማሸነፍ ጉዳይ አሁንም አንድነታችንን በማጥበቅ የምንሰለፍበትና ለበለጠ ድል የምንሽጋገርበት ጊዜ ነው። በዚህ ወቅት በሀገራችን ላይ የሚሰነዘሩ ጥፋቶችና ጥቃቶች ሙሉ በሙሉ ቆመዋል ብለን የምንቀመጥበት አይደለም። በተለያየ ዐውድና መልክ በጠብ አጫሪነት፣ በአቀናባሪነት እና እጅግ ዘግናኝና አሳዛኝ ጥፋቶችን ለማስቀጠል የማይቆፈሩ ጉድጓዶች፣ የማይፈነቀሉ ድንጋዮች እና ሙከራዎች የሉም። ይህን በዘላቂነት ለመመከት እና አስተማማኝ ሰላም ለመገንባት በተግባር ያሻገረን አንድነትና የጋራ አሸናፊነት አሁንም መጎልበትና መጠናከር ይኖርበታል።

በዚህ ወቅት በሀገራችን ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶችና ጥፋቶች ለአንዴም ላይደገሙ ይህን ለማክሸፍ፣ ለመመከት፣ ስጋት እንዳይሆን ለማድረግ፣ የደረሱ ስብራቶችን ማለትም የኅሊና፣ የሞራል እና የማኅበራዊ መስተጋብሮች ለመጠገን፣ መሠረተ-ልማቶችን መልሰን ለአገልግሎት ለማብቃት፣ እና ሁሉንም ጉዳቶች ለመገንባት ከመቼውም ጊዜ በላይ መረባረብ ይኖርብናል።

በዚህ ወቅት በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚሰነዘሩብንን ጥቃቶች ለመመከት በሁሉም መስክ መዝመት፣ መሰለፍ እና ውጤታማ መሆን ያስፈልጋል። መከላከያ ሠራዊታችን እና ልዩ ልዩ የፀጥታ ኃይሎች ከሕዝብ ጋር ሆነው ያንን ስጋት እና እጅግ ሰፊ ጉዳት የቀለሱበትን መንገድ ጠብቀን በሌሎች ግምባሮችም ለስኬታማነት መረባረብ አለብን። የጦርነት ግምባሮቹ እጅግ ብዙ ናቸው። የዲፕሎማሲ ግንባታ ግምባር አለ፤ በኢኮኖሚ ግምባታው ማዕቀፍ ውስጥ ደግሞ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓትን በውጤታማነት መምራት ትልቁ ግንባር ነው።

ከዚህ አንጻር ወደፊትም ሆነ ወደኋላ ኢትዮጵያን ከነጻነት እና ከክብሯ ውሀ ልክ ለአፍታ ለመውረድ የሚደረግ ሙከራን የማናስተናግድበት ጊዜ በመሆኑ በኢኮኖሚው፣ በሰላም ግንባታው፣ በአብሮነት እና ሁሉንም ግንባሮች ይዞ በመራመድ በውጤታማነት መምራት ያስፈልጋል። በዚህ ጊዜ አካሄዳችን ማስገንዘብን፣ ማለዘብን፣ ለኢኮኖሚ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መረባረብን፣ በየትኛውም አቅጣጫ በሀገራችን ላይ የሚቃጣ ድፍረት እና ጥቃትን በበቂ ሁኔታ የመመከትን ጉዳይ አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል።

በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የገቢ ተቋማችን (ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ጉምሩክ ኮሚሽን እና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት) በራሳቸው ዐውድ የተሰማሩበት ሥራም በእጅጉ የሚያኮራና የሚያበረታታ ሆኖ አግኝተነዋል። ይህ የተጀመረው ሁላቀፍ የታክስ አሰባሰብ ርብርብ ሕገ-ወጦችን እና ኮንትሮባንዲስቶችን በመከላከል ሕግን ማስጠበቅ፣ ሥርዓቶችን በእጅጉ ማፅናት፣ መገንባት እና ማስፋት ያስፈልጋል። ይህን ውጤታማ ለማድረግ ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊሆን ይገባዋል።

ይህ ሚኒስቴር መ/ቤት፣ ኮሚሽን እና ተቋማቱ በዚህ አቅጣጫ የያዙት ጉዞ በእጅጉ የሚያበረታታ እና የሚያኮራ ነው። ግብርን በታማኝነት እና በቅንነት ለሚከፍሉት ግብር ከፋዮች እውቅና በመስጠት፣ ከነርሱ ጋር በመሆን እና እነርሱን በቅንነት በማስተናገድ ሀገርን ለማገልገል እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ በእጅጉ የሚያኮራ እየሆነ መጥቷል። ይህ ጉዳይ በአንድ ወቅት በዘመቻ እና በዕድል ፈንታ የተገኘ ሳይሆን ከዓመት ዓመት ተመሳሳይ እና አዳጊ አፈጻጸም እየታየ ነው።

ከ2012 በጀት ዓመት በፊት የተጣሉ መሠረቶች በ2012 የታየው ዕድገት እና አሁን እውቅና እየሰጠነው ያለው አመርቂ አፈጻጸም፤ ከርሱ ጋር ተያይዞ ደግሞ በዚህ ጦርነት ውስጥ በሁሉም አቅጣጫ ባለመረጋጋት ዐውድ ውስጥ ሆነን የዚህ የ2014 የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈጻጸም በስኬት ጎዳና ላይ በመሆኑ ተቋሙ ምን ያህል በጥንካሬ መሠረት ላይ እየተገነባ እንደሆነ መመልከትና መውሰድ ይቻላል። ይህን እጅግ ፈታኝ ጊዜና ወቅት ለመሻገር የጀርባ አጥንት ሆኖ የሚያገለግለን እና የሚያሻግረን ኢኮኖሚው ነው። በኢኮኖሚው ውስጥ ደግሞ ገቢን የመሰብሰብ አቅም ማሳደግ፣ በእቅድ መፈጸም እና ከዚያ በላይ የሚደረግ ጥረት እጅግ በጣም ወሳኝ ነው።

ከዓመት ዓመት እያደገ የመጣው በንጽጽር የላቀ እየሆነ የሚታየውና ለዚህ የበቃነው እንዲሁ በዋዛ የተገኘ ሳይሆን በአመራሮች ጠንካራ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት፣ በአርዓያነት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉም ሠራተኞች በአንድ ልብ በመዝመታቸውን እና በዙሪያቸው የሚታዩ ጥንካሬዎችና ጉድለቶችን እያረሙ ለመጓዝ በመብቃታቸው ነው።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የመንግሥት መ/ቤቶችን የስድስት ወራት አፈጻጸም ሲገመግም በኀላ መልኩ የላቀና የተሻለ አፈጻጸም ካሳዩት ከጥቂት ሚ/ር መ/ቤቶች አንዱና ዋነኛው የገቢዎች ሚኒስቴር ነው። ይህ ድል ከዚህ ታላቅ ሀገር፣ ሰፊ ሕዝብና ሰፊ የኢኮኖሚ መሠረት ከዚህ በላይ ገቢ መሰብሰብ፣ ግብርን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን የማሳደግ፣ በጽኑ መሠረት ላይ የመገንባት፣ የአንድ ዜጋ የህሊና እርካታ ማጠንጠኛ መርሁ ከግብር ኃላፊነት ከግብርን በኃላፊነት መወጣት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የበለጠ ብዙ መሥራት እንዳለብን ያመለክታል።

ጠንካራ ኢኮኖሚ የገነቡ እና ዓለምን የሚዘውሩ ሀገሮች አንዱ የስኬታቸው ምንጭ በገቢ ላይ ያላቸው ውጤታማነት፣ የአስተሳሰብ አንድነት እና የትውልድ ቅብብሎሽ ነው። ይህን ታላቅ ሀገርና ሰፊ ሕዝብ በሁሉም አቅጣጫ የሚሰነዘሩበትን ጫናዎች ጎልብቶ ለመሻገር እና ለመዝለቅ ከተፈለገ ማጠንጠኛው ጠንካራ ኢኮኖሚ ነው። የጠንካራ ኢኮኖሚ ምንጩ ደግሞ ውጤታማ የሆነ የግብር ሥርዓት መገንባት ነው።

የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የጉምሩክ ኮሚሽን እና ሌሎች ሠራተኞች ከዚህ አግባብ ትክክለኛ መንገድ ይዛችኋል፤ በውጤት መረማመድም ጀምራችኋል። ነገር ግን ኢኮኖሚው ሊያመነጨው ከሚችለውና ከምንመኘው አኳያ ሥራችን ገና ጅምር ስለሆነ ለበለጠ ትጋትና ውጤታማነት መታጠቅና መሰለፍ ይኖርባችኋል። ከዚህ አኳያ መንግሥታችን ለዚህ ተቋም ትኩረት የመስጠት፣ ተገቢ የአመራር ድጋፍ የማድረግ፣ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ሥራዎችን አጠናክሮ ይቀጥላል።

ባለድርሻ አካላት፤ ገቢዎች ብቻውን ከመነሻ እስከ መድረሻ ሁሉንም ሊያከናውን አይችልም። ብዙ ተዋንያን አሉና ሁሉም አንድ ላይ መዝመት አለባቸው። ይህን ይዘን ከተጓዝን እንቅፋቶቻችንን እንሻገራለን፤ ከየአቅጣጫው የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን በዘላቂነት እናሸንፋለን።

የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ደረጃ አሸናፊነቱን አረጋግጧል። ቀሪ ዕዳዎቻችን እና የትንኮሳ ፍላጎቶችን አሁንም ቢሆን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመሻገር ብዙ ጥረቶችን እና የአካሄድ አቅጣጫዎችን አጥብቆ ይዟል። ከጀርባ የደጀን ጥንካሬ፣ የሀብት አሰባሰብ፣ የሀብት አስተዳደር ጥንካሬ ደግሞ የሁሉም ሥራችን ማጠንጠኛ ይሆናልና ይህን እውን ለማድረግ የጀመራችሁትን ጉዞ አጠንክሩ። በዚህ በያዝነው መርካት አይገባም። ወደላቀ ከፍታ ለመጓዝ አመራራችሁን አጠንክሩ፤ የሥራ ባህላችሁንም አስፉ። ተያይዘን ኢትዮጵያ የምትከበርበት፣ ድምጻችን የሚሰማበት፣ ከታሪካችን ገናናነታችንን በዘመኑ ተወዳዳሪነት በበለጠ አጎልብተን የምንሸጋገርበት ዘመን ነውና ለዚሁ ስኬት የሁላችንም ጥረት ያስፈልጋል። ጥሩ ይዛችኋል፤ ከሠራነው ያልሠራነው ይበልጣል፤ ለመጪው ዘመን ደግሞ የተሻለ ፈጽማችሁ ተሸላሚ ለመሆን ያብቃችሁ።




## የገቢዎች ሚኒስትር ሰቶ ላቀ አያሌው ንግግር

ሁላችንም እንደምንገነዘበው የአከፋፈል ሁኔታው፣ የክፍያው ዓይነት፣ ስያሜውና የአስተዳደር ሥርዓቱ ቢለያይም ግብር በረጅሙ የአገራችን ታሪክ ውስጥ የነበረ፣ ዛሬም የአሠራር ሥርዓቱ ተሻሽሎና ተጠናክሮ የሚገኝ፣ ወደፊትም የሚቀጥል የአገራት ሁሉ የጀርባ አጥንት ነው። በአገራችን በታክስና በቀረጥ መልክ የምንሰበስበው ገቢ አገራዊ የልማት ወጪያችንን ለመሸፈን ብቻ ሳይሆን ፍትሐዊ የገቢ ክፍፍል ለማስፈን፣ የወጭ ዕቅዱ ከገቢው ጋር ተጣጥሞ የሚሄድበትን መንገድ በማመቻቸት የአገራችንን ፊሲካል ፖሊሲ በአግባቡ ለመምራት እና ከሌሎች የመንግሥት ፖሊሲዎች ጋር ተቀናጅቶ የግሉን ክፍለ-ኢኮኖሚ ለማነቃቃት በሚያስችል መንገድ ታስቦ እየተሠራ ነው። ይህ ወሳኝ እና ትልቅ አገራዊ አደራ ማለትም ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጠው ለገቢዎች ሚኒስቴርና ለተጠሪ ተቋማቱ ነው።

በዚህ ሀገራዊ ኃላፊነት መሠረት በ2013 በጀት ዓመት 290 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 279.4 ቢሊዮን ብር ወይም የእቅዳችንን 96.4 ከመቶ መሰብሰብ ተችሏል። ይህ የእቅድ አፈጻፀም ከ2012 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻፀር 45.7 ቢሊየን ብር ወይም የ19.6% እድገት አለው። ይህ የገቢ አሰባሰብ አፈጻፀም ከነበረው አጠቃላይ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ሁኔታ አንጻር በተለይ የኮሮና ወረርሽኝ ያደረሰውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ተቋቁመን፤ በአሸባሪው ሕወሓት በተከፈተው አገር የማፍረስ ጦርነት ብዙ አካባቢዎች ከሥራ ውጭ ሆነውና በሰሜኑ የአገራችን አካባቢ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶችም ሥራ አቁመው፤ በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠሩ ግጭቶች የንግዱ ማኅበረሰብ በሙሉ አቅሙ እንዳይሠራ በተደረገበት፤ በውጭ ምንዛሬ እና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት የገቢ ዕቃዎች በቀነሱበት ወቅት የተሰበሰበ ገቢ በመሆኑ ውጤቱ እጅግ በጣም ጥሩ ነው።

በመሆኑም ሁሉም የተቋማቱ አመራሮችና ሠራተኞች የዚህ መልካም ውጤት ባለቤት መሆናቸው እሙን ቢሆንም በተነጻጻሪነት የተሻሉትን በተቀመጡት መሥፈርቶች መሠረት በመምረጥ ሌሎችንም ወክለው እውቅና እና ሽልማት እንዲያገኙ ማድረግ የሚያንሳቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይደለም።

በመሆኑም ለዚህ እውቅና እና ሽልማት የበቃችሁ አመራሮችና ሠራተኞች እንዲሁም ተቋማት በሙሉ በራሴና በገቢዎች ሚኒስቴር ስም እንኳን ደስ አላችሁ።

ለዚህ እውቅና እና ለሽልማት የበቃችሁ ምስጉን አመራሮችና ሠራተኞች፤ ለአንድ ዓመት ብቻ የምትሸለሙ ሳይሆን ሁሌም መለያ ባህሪያችሁ እንደምታደርጉትና ሌሎች አመራሮችና ሠራተኞች ከእናንተ በመማር ፈለጋችሁን እንዲከተሉ አስተዋፅኦ እንድታደርጉ አደራ የምንሰጥበት መርሐ-ግብር ጭምር እንደሆነ አሳስለሁ።

የውኃ ጠብታዎች ሲሰበሰቡ ምንጭ፣ ጅረት፣ ወንዝ ሆነው ባህር ይፈጥራሉ እንደሚባለው ሁሉ ሥራችንን፡-

- በእውቀትና በክህሎት፣ በሕግና በሥርዓት ከሠራን፤
- ለህሊናችን ታማኝና ለሕግ ተገዥ ከሆን፤
- የአገርን ሀብት ከብክነትና ከጥፋት ከተከላከልን፤
- ደምበኞቻችንን በታማኝነትና በቅንነት ካገለገልን፤
- ከሙስናና ከብልሹ አሠራር ራሳችንን ካራቅን፤
- ከጥቅመኝነትና ከወገንተኝነት፣ ከአድ ሏዊነትና ከኢ-ፍትሐዊነት ራሳችንን አፅድተን በተገቢው መንገድ ሠርተን ከጨረስብ እና ትናንሽ መጠን ካላ ቸው ብሮች ጀምሮ ገቢን በአግባቡ የምንሰበስብ ከሆነ አገራችን በብድርና በእርዳታ ሰጭ አገሮች እጅ አትወድቅም፤ የልማት ወጭዋንም በራሷ ገቢ ለመሸፈን ያስችላታል።

የልማት ወጭያችንን በራሳችን ገቢ መሸፈን የምንችል ከሆነ ደግሞ ሆስፒታሎች፣ ት/ቤቶች፣ መንገዶች፣ ግድቦች፣ የቴሌኮም፣ የኤሌክትሪክና መሰል መሠረተ-ልማቶች እየተገነቡ፣ ድህነትና ኋላቀርነት እየጠፋ፣ ልመና እና እርዳታ እየቀነሰ ይመጣል ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ከበለፀጉ አገሮች ተርታ አንዷ መሆኗ አይቀርም።

ስለዚህ፤ የሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የተጠሪ ተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች እያንዳንዷን አገራዊ ገቢ በሕግና በአሠራር መሠረት በትጋትና በቁርጠኝነት እንዲሁም በንጹህ እጅ በሰበሰብን ቁጥር እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ዜጋ እያበለፀግን መሆኑን መረዳት አለብን። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የተቋማችን እሴቶች የሆኑትን አገልጋይነት፣ መስጠት፣ ሙያዊ ብቃት፣ ታማኝነትና በቡድን መሥራት በሚል የተቀመጡትን በትክክል ተግባራዊ ካደረግናቸው ከምናስበው ግብ ላይ ያደርሱናል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ፤ ደግሞም እንችላን።

የገቢዎች ሚኒስቴርና የተጠሪ ተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች ሁሉንም ተግዳሮቶች ተቋቁመው የተሻለ ገቢ እንዲሰበሰብ ያደረጉት ከልብ የመነጨ አገራዊ ስሜት ቢኖራቸው እንጂ ሰበቦችን ለማብዛትና ምክንያቶችን ለመደርደር ወቅቱ የተመቸ ነበር። ነገር ግን ይህን አለማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን በእረፍት ቀናቸው፣ ጠዋትና ማታ፣ እሁድና ቅዳሜ ጭምር ያለ እረፍት ብዙዎች ሠርተዋል። በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮችና ሠራተኞች በየመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ሳምንቱን ሙሉ ለ24 ሰዓታት መሥራት ብቻ ሳይሆን ሕይወትና አካላቸውን ገብረዋል። በዚህ መርሐ-ግብርም ስድስት ሠራተኞች የአገርንና የሕዝብን ሐብት ከዘረፋ ለማዳን ሲሉ ከኮንትሮባንዲስቶች ጋር ባደረጉት ግብግብ ሕይወታቸው ያለፈ በመሆኑ እነሱንም በክብር የምናስታውስበት ቀን ነው።

የእነዚህን ጀግኖች ቤተሰቦችም በአንድ ቀን እውቅና በመስጠት ብቻ አስታውሰን የምናልፈው ሳይሆን ተቋማዊ በሆነ መንገድ በቀጣይነት የምንደግፍበትን ሥርዓት ለመዘርጋት በዝግጅት ላይ ነን። በመሆኑም አገራዊ ገቢው የተሰበሰበው እውቀት፣ ጉልበትና ጊዜ ወጥቶበት ብቻ ሳይሆን አካል ጎድሎበትና መተኪያ የሌለው ሕይወት ተከፍሎበት ጭምር መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ።

የተቋማችን አመራሮችና ሠራተኞች መደበኛ ሥራቸውን በአግባቡ ከመሥራት ጎን ለጎን ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት በኩልም የበለጠ መኅልበት ያለባቸው ብዙ መልካም ሥራዎች እየሠሩ ነው። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፡-

- በየወሩ ከወር ደምወዝ በመቁረጥ ከ200 በላይ ወገኖችን በቋሚነት እንረዳለን፤
- ከ112 በላይ ቤቶችን በማደስ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወገኖች በማስረከብ ላይ እንገኛለን፤
- በየጊዜው ደም እየለገስን ነው፤
- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት በየጊዜው ከሚይዛቸው የኮንትሮባንድ ቁሳቁሶች መካከል ለሰው ሠራሽና ለተፈጥሮ አደጋ የተጋለጡ ወገኞችን ሕይወት ለመታደግ የሚያስችሉትን ፈጥነን እያደረስን እንገኛለን፤
- አመራሮችና ሠራተኞች የወር ደምወዛችንን ገበታ ለአገርና ለመከላከያ ሠራዊት አዋጥተናል፤
- ከ100 በላይ ሠራተኞች አሸባሪውን የሕወሓት ኃይል ለመመከት በቀጥታ ወደ ግምባር በመዝመት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

በአጠቃላይ፤ መደበኛ ሥራዎችንም ሆነ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት እንዲያስችል እንዲሁም መሪዎች ጊዜያዊ ተቋም እንዳይሆኑና ቀጣይነት ያለው በደምበኞቻችንም ሆነ በሠራተኞች እምነት የሚጣልበት ተቋም ለመገንባት ጥረት እየተደረገ ነው። ጥረታችንንም የበለጠ አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

የተቋሞቻችን አመራሮችና ሠራተኞች የምንፈራ ሳይሆን በመልካም መስተንግዷችን ምክንያት የምንከበር፤ ከደንበኞቻችን ጋር ስንገናኝ ‹‹መጣብኝ›› ወይም ‹‹መጣችብኝ›› የምንባል ሳይሆን ‹‹መጣልኝ›› ወይም ‹‹መጣችልኝ›› በሚል በተገልጋይነት ስሜት በፈገግታ እንዲቀበሉን የሚያደርግ ገቢራዊ ሥራ መሥራት አለብን።

**በመሆኑም፡-**

- በሕዝብ ወንበር ላይ የተቀመጥነው ሕዝብን ለማገልገል መሆኑን ሁሌም አለመዘንጋት፤
- በሕዝብ ገንዘብና ጊዜ የራሳችንን ከርስና ኪስ ሳይሆን የእምዬ ኢትዮጵያን ቋትና ጎተራ መሙላት፤
- ደምበኞቻችንን ከወገባችን ጎንበስ፣ ከአንገታችን ቀለስ ብለን ማገልገል፤ ደመወዝ የሚከፍሉን እነሱ መሆናቸውን በመረዳት ከማኮሰስና ከማንገላታት ይልቅ ንጉሦቻችን መሆናቸውን በቃላት ሳይሆን በተግባር ማሳየት፤
- ሥራን ዛሬ መጨረስ እንጂ ለነገ ብሎ አለማሳደር፤ ጉዳዮችን አለማንዛዛትና ባለጉዳዮችን አለማጉላላት፤
- ስንፍናንና ልግመኝነትን ማስወገድ፤
- እንደ ወረርሽኝ በሽታ ከተስፋፋው በጉቦ፣ በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በጥቅም ትስስርና አካባቢን መሠረት ካደረገ ሥራ በመቆጠብ እኛ የምንመራቸው ተቋማት ለሁሉም ዜጎች እኩል መገልገያ መሆናቸውን ተገንዝበን መለኪያ መሥፈርታችን ሕግና የአሠራር ሥርዓቱ ብቻ መሆኑን በመረዳት የሚከለክለውን ሕግ መርጦ ማንበብና መተግበር ሳይሆን የሚፈቅድውንም ማየት፤ እንቅፋት የመፍጠር ሳይሆን መንገዶችን የመጥረግ፣ እሾሆችን የመልቀም ሥራ መሥራትን ላፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም።

በአጠቃላይ፤ ተቸግረውና ከእኛ መፍትሄ ፈልገው ባለጉዳዮች ሲመጡ መርዳትና ማገዝ፣ በቅን ልቦና እና በንጹህ እጅም መሥራት ይኖርብናል። ይህ የሚሆን ከሆነ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ስለተቋሞቻችን በአደባባይ ይመሰክራሉ። የመጨረሻው የስኬታችን መለኪያ መስፈርትም የእኛ የአደባባይ ዲስኩር ሳይሆን የሕዝባችን የምስክርነት ቃል ይሆናል።

የ2013 በጀት ዓመት ስኬትና ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ በ2014 በጀት ዓመት 360 ቢሊዮን ብር እቅድ ይዘን እየሠራን ሲሆን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ሆነንም ቢሆን የስድስት ወራት አፈጻፀማችን የሚያሳየው ስኬትን ነው። ይኸውም በስድስት ወራት ውስጥ 185.7 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 171.3 ቢሊዮን ብር ወይም የእቅዳችንን 92.21% ለመፈፀም ተችሏል። ካለፈው ተመሳሳይ ስድስት ወራት አፈጻጸም አንጻር ሲታይ በብር 22.2 ቢሊዮን ወይም በ14.9% እድገት አለው።

ስለዚህ፤ በቀሪዎቹ ስድስት ወራት የአሠራር ሥርዓታችንን ከማዘመን ባሻገር ለአሠራር ልህቀታችን ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ የአገልጋይነት ሰብዕናን በመላበስ አገልግሎታችንን ተገልጋይ ተኮር፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ቀላል፣ ለደንበኞቻችን መንገድ ቀያሽና ፍሰቱን አሳላጭ እንዲሆን በቁርጠኝነት ልንሠራ ይገባናል። በሌላም በኩል የአሠራር ግድፈቶችንና ችግሮችን ለይቶ በማረምና ዘላቂ መፍትሄ በመስጠት የማስተማርና የአብርሆት ሥራን በመሥራት የአገር ውስጥ ታክስንም ሆነ የወጭ ንግድ ቀረጥና ታክስን ከመቸውም ጊዜ በላይ በመሰብሰብ የውጭ ጠላቶቻችንና የውስጥ ባንዳዎችን ምኞት ከንቱ በማድረግ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነታችንን በጀግንነትና በአርበኝነት ደጋግመን ልናረጋግጥ ይገባል።

በመሆኑም፤ ኮንትሮባንድን፣ የንግድ ማጭበርበርን፣ ግብር ስወራንና ማሸሽን፣ ደረሰኝ አለመቁረጥን፣ ከሐሰተኛ ደረሰኝና ከሐሰተኛ ማንነት ጋር ተያይዞ የሚሠሩ ወንጀሎችን ከሕዝባችን እና አጋር አካላት ጋር በመሆን በመከላከልና በገቢዎች ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የተጀመሩትን የአሠራር ሥርዓቶች የበለጠ በማዘመን ለሕዝባችንና ለአገራችን ታማኝ ሆነን በመሥራት የ2014 በጀት ዓመት እቅድ እንደምናሳካ እምነቴ ነው። ለዚህ ደግሞ በገቢዎች ሚኒስቴርና በተጠሪ ተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች በመተማመን መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ለመላው የአገራችን ሕዝብና አጋር አካላት ደግሞ የተለመደ ትብብራችሁና ባለቤትነታችሁ እንዳይለየን ጥሪዬን አቀርባለሁ። .

# ሕግ-ግብር

አዘጋጅ- ሰዒድ ገልገሉ

ይህ አምድ የታክስ አስተዳደርና የጉምሩክ አሠራር የሚመራበትን ህጎች፣ መመሪያዎችና አሰራሮች፣ ለሕግ ተገዢነት የሚያስተምሩ አስተሳሰቦችን፣ ሕጎችን ለአሠራር ምቹ የሚያደርጉና ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን የሚያጎለብቱ አሰራሮችንና ተሞክሮዎችን የሚያስተዋውቅ ጽሑፍ ይቀርብበታል፡

## የ3 ነጥብ 7 ሚሊዮኑ ብር ቀብድ

ንማጅ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በቁርጥራጭ ብረት አቅራቢነት የሚታወቅ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ግብር ከፋይ ሲሆን በዋና መ/ቤት በታክስ ማጭበርበር ምርመራ ዳይሬክቶሬት የታክስ ኢንተለጀንስ ሥራ ክፍል አማካኝነት ተገቢ ክትትልና የሰነድ ምርመራ ሲደረግበት ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ድርጅቱ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ በሌለበት ሁኔታ ከ13 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ ግዢ ያለ በማስመሰል ሀሰተኛ የወጪ ደረሰኞች ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ወጪዎችን በማወራረድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ በማቀናነስና ተመላሽ በመውሰደ የታክስ ማጭበርበር ወንጀል እንደፈጸመ ስለታወቀ የድርጅቱ ሂሳብ የኢንቨስትጌሽን ኦዲት እንዲከናወንበት ለሚኒስቴሩ የታክስ ኢንቨስትጌሽን ኦዲት ሥራ ክፍል ተመርቶ ነበር፡፡

የተጀመረው የኦዲት ሥራ በሒደት ላይ እያለ ደግፍ ዘብሬ በረካ የተባለ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የታክስ ኢንተለጀንስ ባለሙያ የኦዲት ሥራውን እንዲያከናውን ወደተመራለት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ ኦዲተር በተለያየ ሰበብና ምክንያት በመቅረብ ኦዲተሩ በድርጅቱ ላይ በኢንተለጀንስ ሰነድ ምርመራ ግኝትና በኦዲት ምርመራም ወቅት በራሱ ሊያገኝ ከሚችለው ተጨማሪ የታክስ እዳ ግኝት በኦዲት ውሳኔ ማስታወቂያ ሲያወጣ ዝቅ አድርጎ እንዲያወጣ የማግባባት ሥራ ይሠራል፡፡ ለዚህም ተግባሩ ከንማጅ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ዳጎስ ያለ ገንዘብ እንደሚከፈለው ይነግረዋል፡፡

ደግፍ በድርጅቱ እና በኦዲተሩ መካከል ለሚጫወተው የአዳራዳሪነት ሚና ኦዲተሩ ከሚያገኘው መደለያ ወይም ጉቦ ውስጥ 35 በመቶውን ሊያገኝ ወይም ሊካፈል እንደሚገባ ሊያግባባ ሞክሯል፡፡ በተለያዩ ጊዜያትም ኦዲተሩን የንማጅ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሥራ አሥኪያጅ ከሆኑት አቶ ካሳሁን ለገሰ እና ከሒሣብ ሠራተኛው ከአቶ መላኩ አደራው ጋር በቅደም ተከተል በተለያዩ ቦታዎች አገናኝቶ አደራድሯል፡፡

ደግፍ ዘብሬ፣ የድርጅቱ ባለቤት እና ሥራ አሥኪያጅ በተደጋጋሚ ባደረጉት ግንኙነትና ስምምነትም ኦዲተሩ እያከናወነ ባለው የኦዲት ምርመራ ግኝት ከአምስት እስከ 10 ሚሊዮን ብር ግኝት ብቻ በታክስ እዳ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ እንዲያወጣ፤ በምላሹ ድርጅቱ 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር ጉቦ እንደሚሰጥ፤ ገንዘቡንም ከፋፍለው በካሽ እንደሚከፍሉ የመጨረሻ ስምምነት አድርገዋል፡፡

ይሁን እንጂ የኢንቨስቲጌሽን ኦዲተሩ በተቀናጀ መልኩ በመንግሥት ገቢ ላይ ሊፈጸም የታሰበውን ወንጀል አስቀድሞ በመረዳት ጉዳዩን ገና ከጅምር ለታክስ ማጭበርበር ምርመራ ዳይሬክተር ከሳወቀ በኋላ ከዳይሬክተሩ ጋር በመሆን ለገቢዎች ሚኒስቴር የሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ጥቆማ ሰጡ፡፡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬቱም ወንጀሉን ይፈጽማሉ ተብለው የተገመቱ ተጠርጣሪዎች ክትትል ተደርጎባቸው ለጉዳዩ መፈጸሚያ መደለያ የታሰበውን ገንዘብ ሲቀባበሉ እጅ ከፍንጅ ለመያዝ ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ቢሮ አስቀድሞ ስላሳወቀ ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽኑ በመደባቸው የክትትል ባለሙያዎች እና በሚኒስቴሩ የሥራ ኃላፊዎች አማካኝነት ለአንድ ሳምንት ተከታታይ ቀናት በተደረገ ክትትል ሁለቱም የድርጅቱ ኃላፊዎች ጥር 13/2014 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ክፍያ (ቀብድ) የታሰበውን 198ሺ ብር ይዘው መጥተው በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ኮተቤ ደህንነት በሚባል ሥፍራ ከጠዋቱ 3፡00 አካባቢ በአንድ አነስተኛ ግሮሰሪ ውስጥ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የታክስ ኢንተለጀንስ ባለሙያ ደግፍ ዘብሬ ጋር ሲቀባበሉ እጅ ከፍንጅ ተይዘዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የተደረገው የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ቢሮ ተገቢው የምርመራ ሥራ እንዲከናወን እነዚህን ማስረጃዎች እና ተጠርጣሪዎቹ ያደረጓቸውን የስልክ ልውውጦች የያዘ አንድ ሲዲ ማስተላለፍ ነው፡፡

ይህ ሒደት የሚያሳየን ነገር በርካታ ታማኝ ግብር ከፋዮች እንዳሉ ሁሉ ጥቂት የዚህ ዓይነት ድርጊት ፈጻሚዎችም መኖራቸውን ነው፡፡ በተመሳሳይ፤ እንደ ጠቋሚው የገቢዎች ሚኒስቴር ሠራተኛ በሞሉባት ተቋም እና ሀገር፤ ከሚያገኙት ያልተገባ ጥቅም በላይ ሀገርና ሕዝብን የሚያስቀድሙ ዜጎችም መኖራቸውን ነው፡፡










## ለዘላቂ ድጋፍ መንደርደሪያ እገዛ






የገቢዎች ሚኒስቴር ጥር 21/2014 ዓ.ም. በ2013 በጀት ዓመት የላቀ አፈጻጸም ላሳዩ ሠራተኞች፣ አመራሮች እና አካላት ሽልማትና እውቅና ሲሰጥ የብዙዎችን ስሜት በሀዘንም፣ በደስታም የነካ ሽልማት ለስድስት ሰዎች አበርክቷል፡፡ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የተገኙትን ያሳዘነው በኮንትሮባንድ መከላከል ተግባር ላይ ሳሉ ሕይወታቸው በኮንትሮባንዲስቶች እና በአደጋ ያለፈ ሠራተኞችን ታሪክ ሲሰማ ሲሆን የተደሰተው ደግሞ ለሟች ቤተሰቦች ለእያንዳንዳቸው የ75ሺ ብር ሽልማት ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን እና ከገቢዎች ሚኒስትር ላቀ አያሌው እጅ ሲረከቡ ነው፡፡ በዚህም መሠረት፡-

1. አቶ መልካሙ ዓለሙ ካሣ

ባሕርዳር ላይ የተያዘን የኮንትሮባንድ እቃ ለመፈተሽ ሲዘጋጁ በኮንትሮባንዲስቱ በጥይት ተመትተው ሕይወታቸው አልፏል፡፡

2. አቶ ጋሻው አገኘ ይሁኔ

ለኮንትሮባንድ ክትትል ከወረታ ወደ ባሕርዳር በመጓዝ ላይ ሳሉ በደረሰባቸው የመኪና አደጋ ሕይወታቸው አልፏል፡፡

3. አቶ ዓለሙ ወርቁ ሉሌ

ለኮንትሮባንድ ክትትል ከወረታ ወደ ባሕርዳር በመጓዝ ላይ ሳሉ በደረሰባቸው የመኪና አደጋ ሕይወታቸው አልፏል፡፡

4. አቶ ጥበቡ ዳቢ ዳዲ

የጅግጅጋ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አሽከርካሪ ሲሆኑ ኮንትሮባንዲስቶችን አሳዶ ለመያዝ እየተሠራ ባለው ሥራ ያሽከረከሩት የነበረው መኪና በመገልበጡ ሕይወታቸው አልፏል፡፡

5. ኮንስታብል ንግሥት በየነ ገዲቾ

ቦምባስ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ላይ የኮንትሮባንድ እቃን በመያዝ ላይ ሳሉ ከኮንትሮባንዲስቶች በተተኮሰባቸው ጥይት ሕይወታቸው አልፏል፡፡

6. ምክትል ሳጂን ነስሮ ዋቅጂራ ባልቻ

ቦምባስ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ላይ የኮንትሮባንድ እቃን በመያዝ ላይ ሳሉ ከኮንትሮባንዲስቶች በተተኮሰባቸው ጥይት ሕይወታቸው አልፏል፡፡

መረጃውን የላኩልን የጉምሩክ ኮሚሽን ሰው ሀብት ዳይሬክተር ካሳሁን ኪዳኔ ናቸው፡፡

### የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

### እ ሴ ቶ ች

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)